በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ነሐሴ 30 ቀን 2008 ዓ.ም

# አጠቃላይ የፈተና ወቅት፤ሕዝባዊ አመጹ ይፋፋም!!

በትምህርት ሥርዓት ከአንድ ክፍል እርከን ወደ ሚቀጥለው ለመዛወር ፈተና ተፈትኖ ማለፍ ግዴታ የሚሆንበት አካሄድ አለ። ፈተና የሚሰጠው በንፍቀ ዓመትና በዓመት መጨረሻ ላይ ቢሆንም እንዳስፈላጊነታቸው መለስተኛ ሙከራዎች እየቀረቡ የተማሪዎችን ክህሎት በማገዝ ለዋናው ማዘጋጃነት ይረዳሉ ። በሂደቱ የመምህራን ሚና ዋነኛና ወሳኝ ቢሆንም ተማሪዎችንና የት/ቤቶችን የአስተዳደርና የተለያዩ ባለሙያዎችንም ተሳትፎ ይጠይቃል። ትምህርት የዕድገት መሰረት ነው ቢባልም ያለሕብረተሰቡ ንቁና አመርቂ ተሳትፎ አገር ተረካቢ ትውልድ መገንበቱ ምኞት ብቻ ሆኖ ሊቀር ይችላል።

ከላይ ያለው የዚህ ጽሑፍ ርእስና ለመግቢያ የቀረበው በአንድ መስክ ማለትም ስለትምህርት ስርዓቱና ለተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል የማለፍ ሂደትን ለመተንተን ያለመ አይደለም።ለማቅረብ የታሰበው በሕዝብ ላይ የተጋረጠውን ለ25 ዓመታት ተጠራቅመው የነበሩትን ፈተናዎች የሚመለከቱ ናቸው።

ከ1983 ዓ.ም ግንቦት ወር ጀምሮ በመንግስት ስም በአገዛዝ ላይ የወጣው ወያኔ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ፣ ሁለት ..... እያለ ከወቅትና ከሁኔታዎች አየተማረ ከሚደርስበት የጭቆና አገዛዝ ለመውጣት እየሞከረ 25 ዓመታት በመከራ አረንቋ ዳክሯል፤በችግር ማቋል። እንደአገዛዙ ከፋትና በሕዝብ ላይ አያደረሰ እንዳለው ግፍ ለስርኣቱ 25 ወራትም የሚያደርሰው ዕውነታ አልነበረም። ለዚህ አገር አጥፊ ቡድን ምርኩዝ ሆኖ ያገለገለው በዘር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ነው። ይህ ጣሊያንን ጨምሮ በሩቅና በቅርብ ጠላቶቻችን ተነድፎ የነበረ ለአፍሪቃዉያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት የሆናችውን አገራችንን ለማዳከም፣ ሕዝቡንም በዘር፣ በጎሳና በቋንቋ ለያይቶ የመበታተንና ብሎም የማጥፋት፣ ታርኳ እንዲበረዝ፣ እንዲደለዝ በሁሉም መልኩ ወያኔን በማገዝ በጉዳይ አስፈጻሚነት አሳማሩ። ገና በሽግግር ወቅት በቻርታር ተብዬ የወያኔ ሕገ አራዊት ሰነድ አገሪቱን መግዛት ሲጀምር የህዝብ ውክልናና ይሁንታ የሌላው የሽፍቶች ቡድን የኢትዮጵያ አካል የነበራችውን ኤርትራ ካለም አቀፍ ድንጋጌዎች ውጪ እንድትገነጠል ለውጪ ተባባሪዎች ምቹ ሆኖ በመገኘት ማመልከቻ ለተባበሩት መንግስታት ለማቅረብ የመጀመሪያ ሆነ።ቢያንስ አፈጻጸሙን የኢትዮጵያ ሕዝብ መቃወም ሲገባ በዝምታ ማለፉ የመጀመርያ ፈተና ነው ማለት ይቻላል።

ወያኔ ፖለቲካውን በዘርና በቋንቋ ላይ መስርቶ አገሪቱን በክልሎች ሲከፋፍል አንድ ዜጋ በመረጠበት አካባቢ መኖርና መስራት ሰብአዊ መብት መሆኑ ተጥሶ ዜጎች በአገሪቱ በብዙ ቦታዎች የአካል፣ የሞራል፣ የሕይወትም አደጋ ተጋርጦባቸው አልፏል። የተወሰኑ የሕብረተሰቡ አባላት ይህን ኢሰብአዊ የፖለቲካ አጀንዳ በማራገብ የሕዝቡ የአብሮነት እሴቶች እንዲናጉና የእርስ በርስ ፍጅት እንዲከሰት ሲሳሩ ገና በጧቱ መወገዝ ሲገባቸው የዘረኞቹ አውራ ወያኔና ተከታዮቹ እንዲጎለብቱና ጡንቻቸውን እንዲያሰርፉብን ተመቻናቸው፤ ሌላ ያሳለፈነው ፈተና ሆኖ ቆየ።

ወያኔ የሕዝብን መለያየትና ድክመት እየለካ ፖለቲካውንም ፣ ኢኮኖሚውንም፣ የማህበራዊ እሴቶቻችንንም ጠቅልሎ በመያዝ በተለይ ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ወሳኝነት ይሠራሉ የተባሉ ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶችን ህልውናቸውን ከዶና ድፍጦ የፖለቲካ ምህዳሩን በማጥበብ ጠንክሮ እየሠራ ቆየ።የ1997ዓም ምርጫ ውጤት ለዚህ አብነት ነው። የውጭ ኃይሎች ( አሜሪካና እንግሊዝ)ወያኔ የሕዝብ ድምፅ እንዲቀማ ማገዛቸው ሳይረሳ በተቃዋሚ ስም የተቀመጡ ቡድኖችና ግለሰቦችም ያን ህዝባዊ ግላትና እንቅስቃሴ ቀዝቃዛ ውሃ ሲቸልሱበት ወደፊት ገፍተን ለፈጸሙት ወንጀል ተጠያቂ አለማድረጋችን አንዲሁ ያለፈው ፈተና ነው።

ዳሩ ካልተከበረ መሐሉ ዳር ይሆናል እንዲሉ በአጥንትና በደም የተከበረው ድንበራችን ተደፍሮ መሬታችን ለባዕዳን ሲሰጥ መሆኑ እየተነገረን በቸልታ መቆየታችን ጭራሹን በእንቬስት መንት ስም መሬት መቸቸቡ ደርቶ አዲስ አበባ ዙሪያና ራሷንም አዲስ አበባንም ሲጨምር ባነናል።ይህ ሁሉ ግዙፍ ግፍና መከራ ሲዳራረብ የወያኔ ፕሮፖጋንዳ ልማትና ዕድገት ተብሎ እያደናቆረን ታይቷል። በአጭሩ 25 ዓመታት ኢትዮጵያውያን በሁሉም መስክ አበሳቸውን ያዩባቸው ዓመታት ናቸው።ከዚህም የተነሳ ዜጎች የሚደርሱባቸው ግፎች ከሚሸከሙት በላይ ስለሆነ አዚህም እዚያም ሕዝባዊ ተቃውሞዎች እንደ እሳተ ገሞራ መፈንዳት ጀምረዋል።



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*እነዚህ ሕዝባዊ ተቃውሞች በተለይ ትላልቅ የሕበረተሰቡ አካል በሆኑ በኦሮምና በአማራ አካባቢዎች በሕዝብ የቀረቡ ጥያቄዎች በፍትሐዊ መንገድ መመለስ ሲገባቸው ከመነሻው ለሕዝብ ክብር የማይሰጠው የወያኔ ስርዓት ምላሹ ድብድባ፣እስራት፣ግድያ-----ሆኖ የሕዝቡን ቁጣና ምሬት አባብሶታል። በእነዚህ ሁለት ክልሎች በሕዝብ የተነሱ የመብትና የፍትሕ ጥያቄዎች ድንገት የተከሰቱ ዱብዳ አይደለም። በጋምቤላ፣ በሀዲያ፣ በወላይታ፣ በጌዲኦ ፣ በሲዳማ፣ ሱማሊያ በኮንሶና ሌሎችም አካባቢዎች ዜጎች ባነሷቸው የመብት ጥያቄዎች የዘር ማጥፋትን (Genocide) አካቶ ግድያ ፣ ማሰቃየት ፣ ለስደት መዳረግ ፣ የንብረት ውድመትና ሰቆቃዎች ስለደረሱ የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኙ ይገባል።*

*በዚህ ወቅት ላይ ሆነን ሁኔታዎችን ስንገመግም ለዜጎች ሁሉ ፊት ለፊት የተጋረጠ ትልቅ ፈተና ይታያል።ይህን የፈተና ወቅት ለማለፍ የሚያስችሉ ተመክሮዎችና ልምዶችን ልንጠቀምባቸው ከባጀን ሕዝባዊ ድልን አንጎናጸፋለን።ሥርዓቱንም እናስወግዳለን። ሁላችንም ነፃ እንወጣለን። ያለፉት ተመክሮዎች በግልጽ ያሳየን በጎሳና በቋንቋ መለያያታችን የጠቀመው የጋራ ጠላታችን ለሆነው የወያኔን ሥርአት ነው።*

*ይህን ልዩነት አስወግደን በቅርቡ በአጋአዚ የሚፈሰው ደም በጎንደር ወገኖቻችን እንደተስተጋባው የኦሮሞ ወገኖቻችን ደም ደማችን ነው፣የጋምቤላው፣ የሶማሌው፣ የአፋሩ፣የሲዳማው---------የሚለው ቀጣይ መሆኑና በተግባር ሊገለጽ ከቻለ የተጋረጠውን አጠቃላይ ፈተና ማለፍ አያዳግትም ፤ ነፃነትም ይረጋገጣል፤ ይህ ነው ብሄራዊ አንድነታችን። ይህ ሲሆን ከግለሰቦች ፣ ከቡድኖች ባጠቃላይ ከዜጎች እየቀረበ ያለው ያገር አድን ጥሪ በድል ይጠናቀቃል።ይህ ዕድል ዕውን እንዲሆን እስካሁን መሰናክል የሆኑብን ወያኔ የፈጠራቸው የከፋፍለህ ግዛ ሴራዎች ከሰመው ሁላችንም በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር መሰባሰብ ስንችል እንደሆነ አያጠራጥርም ። ያንዱ ቤት ሲቃጠል ሌሎች ተረባርበው ካለጠፉት እሰቱ ወደ ሌላ አካባቢ ሁሉ መዛመቱ አይቀርም። በመሆኑም በጋራ ተነስተን የጋራ ጠላታችንን ወያኔን እናስወግድ።*

*በአሁኑ ጊዜ ኦሮሚያ፣ አርባምንጭ ፣ ኮንሶ በወታደራዊ አገዛዝ ስር ወድቀዋል። የውጪ ኃይል የተከበበ ይመስል ወያኔ ታንክና መድፍ ሳይቀር በአማራው ሕዝብ ላይ አስማርቶ ጫካ በነበረበት ወቅት ይህን የሕብረተሰብ ክፍል ለማጥፋት በፖሊሲ ደረጃ ያስቀመጠውን ተግባራዊ እያደረገ እንደሆነ ያመለክታል።የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ሁኔታ ለመቀየር በሁሉም መስክ ትግሉን ማጠናከር ፣ ወዳጅ - ጠላቱን መለየት ይጠበቅበታል። ትግሉም በአስመሳዮች እንዳይጠለፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ሕዝባዊ አመጹ ማፋፋም ይኖርበታል።*

*በ1966 ዓ.ም ከአውሮፓና ከአሜሪካ የተወጣጡ የዲያስፖራ ፖለቲካኞች ደርግ አብዮተኛ ነው፤ ሂሳዊ ድጋፍ በመስጠት አብረን መስራት እንችላለን በማለት ከፋሺታዊ ደርግ ጋር በማበር ሕዝባዊ አመጹ እንዲኮላሽ ከፍተኛ ድርሻ እንዳበረከቱ የትናንት ትውስታ ነው።በተመሳሰሳይ ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ ዛሬም በመግለጫ ጋጋታ የታጠሩ የዲያስፖራ ፖለቲካኞች ቀደም ብለው ከወያኔ ጋር አብረው ይሠሩ ከነበሩ ግለሰቦች ጋር በመሆን በባዕዳን ኃይሎች አስተባባሪነት ወያኔን ያካተተ የሽግግር መንግስት ለመመስረት ደፋ ቀና እያሉ ነው። ይህ አካሄድ በአሁኑ ወቅት እየተቀጣጠለ ያለውን ሕዝባዊ አመፅ ለማኮላሸትና ወያኔ ነፍስ እንዲዘራ ለማድረግ ነው። እየተቀጣጠለ ያለው ሕዝባዊ አመጽ ከዳር እንዲደርስ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ድጋፉን ይሰጣል፤የበኩሉንም አስተዋጽኦ ያዳርጋል።*

*መምህራን በ1966 ዓ.ም ያካሄዱትን አገር አቀፍ የስራ ማቆም አድማ በመጪው 2009 ዓም እንዲደግሙት ማህበሩ ጥሪ ያቀርባል።እየተቀጣጠለ ያለውን ሕዝባዊ አመጽ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር በመሆን በስልት ሕዝቡን በማደራጀትና በመቀስቀስ ታሪካዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ያሳስባል። በአጠቃላይ ተማሪዎች ፣ ወላጆች ፣ ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲ ቀርጾ በትምህርቱ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ወንጀል በመፈጸም ላይ የሚገኘው የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ላይ ጦርነት አውጇልና አገርና ሕዝብን ለማዳን በጋራ የጋራ ጠላታችሁ በሆነው ወያኔ ላይ እንዲትነሱ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በድጋሚ ጥሪ ያቀርባል።*

*ነፃነት ወይም ባርነት ምርጫ ሆኖ ቀርቧል!!*
*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!*
*ሕዝባዊ አመጹ ይፋፋም!!*